የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፲፮
አዲስ አበባ—ጥር ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፬

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

8th Year No. 16
ADDIS ABABA-31st January, 2002

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፷፱/፲፱፻፺፬ ዓ.ም
የኢትዮጵያ የገጠር ኢነርጂ ልማትና ማስፋፊያ ማዕከል ማቋቋሚያ አዋጅ ........................................ ገጽ ፩ሺ፯፻፯

## CONTENTS

Proclamation No. 269/2002
Ethiopian Rural Energy Development and Promotion Center Establishment Proclamation ........ Page 1707

### አዋጅ ቁጥር ፪፻፷፱/፲፱፻፺፬
### የኢትዮጵያ የገጠር ኢነርጂ ልማትና ማስፋፊያ ማዕከልን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

አገሪቱ የምትከተለው ገጠሩን ማዕከል ያደረገ የኢኮኖሚ ፖሊሲ በመሆኑ እና በዚህም ፖሊሲ መሠረት የገጠሩን ዘላቂ የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማረጋገጥ የኢነርጂ ልማት ወሳኝ በመሆኑ፤

ለገጠሩ ተስማሚ የሆኑ የኢነርጂ ምንጮችና ቴክኖሎጂዎች ጥናትና ልማት ሥርዓት ባለውና በተቀናጀ ሁኔታ መካሄድ ያለበት በመሆኑ፤

በአካባቢ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድረውን ልማዳዊ የኢነርጂ አጠቃቀም በዘመናዊ ዘዴ መተካት አስፈላጊ በመሆኑ፤

እነዚህን ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ ተገቢው ሥልጣንና ተግባር ያለው አንድ ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ የገጠር ኢነርጂ ልማትና ማስፋፊያ ማዕከል ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፷፱/፲፱፻፺፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል።

፪· ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

፩· "ኢነርጂ" ማለት ከባዮማስ ፣ ከውኃ ፣ ከጂኦተርማል፣ ከፀሐይ ፣ ከነፋስ ፣ እንዲሁም ታዳሽ ካልሆኑ እንደ ነዳጅ፣ ማዕድናት የመሳሰሉ ምንጮች እና ከሌሎች የተለያዩ ቁሳቁሶች የሚገኝና ለገጠሩ ኅብረተሰብ የሚያገለግል ኃይል ነው፤

### *PROCLAMATION NO. 269/2002*
### *A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIAN RURAL ENERGY DEVELOPMENT AND PROMOTION CENTER*

*WHEREAS,* the country is following rural-based economic policy; and the development of energy plays a decisive role in ensuring sustainable socio-economic progress of the rural areas;

*WHEREAS,* it is essential to undertake the study and development of energy resources and technologies suitable for the rural areas in a systematic and coordinated manner;

*WHEREAS,* it has become necessary to substitute with modern methods the traditional energy utilization system which has caused negative impact on the environment;

*WHEREAS,* to attain these objectives, it has become necessary to establish an autonomous federal government organ conferred with appropriate powers and duties;

*NOW, THEREFORE,* in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Ethiopian Rural Energy Development and Promotion Center Establishment Proclamation No. 269/2002,"

2. *Definitions*

Unless the context requires otherwise, in this Proclamation:

1) "Energy" means power generated from biomass, water, geothermal, sunlight, Wind, non-renewable resources like petroleum or minerals and other various materials used for rural communities.

፪· "ሚኒስትር" እና "ሚኒስቴር" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የገጠር ልማት ሚኒስትር እና ሚኒስቴር ነው።

፫· *መቋቋም*

፩· የኢትዮጵያ የገጠር ኢነርጂ ልማትና ማስፋፊያ ማዕከል / ከዚህ በኋላ "ማዕከል" እየተባለ የሚጠራ/ ራሱን የቻለና የሕግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪· ማዕከሉ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

፬· ዋና መሥሪያ ቤት

የማዕከሉ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ሊኖሩት ይችላል።

፭· ዓላማ

የማዕከሉ ዓላማ ለገጠሩ የሚያገለግሉ የኢነርጂ ምንጮች እና ቴክኖሎጂዎች የሚለሙበትንና የሚስፋፉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይሆናል።

፮· የማዕከሉ ሥልጣንና ተግባር

ማዕከሉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩· ለገጠሩ ተስማሚ የሆኑ የኢነርጂ ምንጮችን መለየት እና ለልማት የሚረዳ ጥናት ማካሄድ፣

፪· ከውጭ ሀገር የሚገኙትን የኢነርጂ ቴክኖሎጂዎች ከአገሪቱ ፍላጎት ጋር በማጣጣም ማላመድ እና አገር በቀል የኢነርጂ ቴክኖሎጂዎችን ማበልፀግ፣

፫· የኢነርጂ ጥናት ሥራዎችን ማስተባበር ፤ ማበረታታት እና መደገፍ፣

፬· የገጠሩን የኢነርጂ ፍላጎት ፤ አቅርቦት እና ፍጆታ ማጥናት እና በየጊዜው መረጃ ማጠናቀር፣

፭· የአካባቢ ጥበቃን ከግምት ውስጥ የሚያስገቡ፣ ተመጣጣኝ ዋጋና ብቃት ያላቸውን የኢነርጂ ምንጮችና ቴክኖሎጂዎች ልማት ፤ ሥርጭት ፤ አጠቃቀም ቁጠባ ማጥናት እንደነገሩ አግባብነት በግል ባለሀብቶች ፤ በመንግሥትና በሌሎች ዘርፎች በኩል ለገጠሩ ኅብረተሰብ ማስተዋወቅ፣

፮· የተለያዩ የኢነርጂ ምንጮችና ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም የሚያስከትለውን ማኅበራዊ ፤ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ተጽዕኖ መገምገም፣

፯· በኢነርጂ ዘርፍ እንደአስፈላጊነቱ በክፍያ ወይም ያለክፍያ የማማከር አገልግሎት መስጠት፣

፰· የኢነርጂ ጥናትን በሚመለከት መረጃ መሰብሰብ፣ በባለቤትነት መያዝ ፤ እንደአስፈላጊነቱ ዋጋ በማስከፈል ወይም ያለክፍያ ለተጠቃሚዎች ማቅረብ ፤ እንዲሁም መጽሄቶችን ማዘጋጀትና ማሠራጨት፣

፱· ከሥራው ጋር አግባብ ያለውን መረጃ ሁሉ ከማንኛውም ምንጭ መጠየቅና ማግኘት፣

፲· የኢነርጂ ልማት፣ ሥርጭት፣ አጠቃቀምና ቁጠባን በተመለከተ የገጠሩን ሕብረተሰብ ግንዛቤ ማዳበር ፤ ሥልጠና መሥጠትና እንዲሁም ከክልሎች ጋር መተባበር፣

፲፩· ከሥራው ጋር አግባብነት ባላቸው የኢነርጂ ጥናት እና ምርምርን በሚመለከቱ ማናቸውም ግንኙነቶች ከሌሎች ጋር በመተባበር መሳተፍ እንዲሁም ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ከአገር በቀል፣ ከውጭ አገር እና ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር መተባበር፣

፲፪· የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ መክሰስና መከሰስ፣ እና

፲፫· ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ሕጋዊ ተግባራትን ማከናወን።

፯· የማዕከሉ ድርጅታዊ አቋም

ማዕከሉ፣

፩· በመንግሥት የሚሾም አንድ ዋና ዲሬክተር፣ እና

፪· አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል።

፰· የዋናው ዲሬክተር ሥልጣንና ተግባር

፩· ዋናው ዲሬክተር የማዕከሉ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ ከሚኒስትሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የማዕከሉን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።

2) "Minister" and Ministry" means the Minister and Ministry of Rural Development respectively.

3. *Establishment*

1) There is hereby established the Ethiopian Rural Energy Development and Promotion Center (hereinafter "the Center") as an autonomous Federal Government organ having its own juridical personality.
2) The Center shall be accountable to the Ministry.

4. *Head Office*

The head office of the Center shall be in Addis Ababa and may have branch offices else where as may be necessary.

5. *Objectives*

The objectives of the Center shall be to make conditions convenient for the development and promotion of rural energy resources and technologies.

6. *Powers and Duties of the Center*

The Center shall have following Powers and duties:

1) identify the enegry resources suitable for the rural areas and conduct studies for their development;
2) adapt foreign energy technologies in line with the needs of the country and improve indigenous energy technologies;
3) coordinate, encourage and assist energy study activities;
4) study the energy demand, supply and consumption patterns of the rural areas and compile data periodically;
5) study the production, distribution, utilization and conservation of affordable and efficient energy resources and technologies with due regard to the protection of the environment and promote same to the rural community via private, public and other sectors as the case may be;
6) evaluate the social, economic and environmental impacts of using various energy sources and technologies;
7) provide consultancy services in the energy sector with or without payment as the case may be;
8) collect and own information related to energy studies, and may make it available to users with or without payment as the case may be and also publish and distribute journals;
9) require and obtain any information, relevant to its activities, from any sources;
10) raise the awareness of the rural community and provide trainings concerning the production, distribution, utilization and conservation energy; and cooperate with regions;
11) In cooperation with others participate in all communications on energy studies and researches related to its activities, and co-operate with local, foreign and international organizations for the attainment of its objectives;
12) own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name;
13) perform such other lawful activities as may be necessary for the attainment of its objectives.

7. *Organization of the Center*

The Center shall have:

1) A Director General to be appointed by the Government; and
2) the necessary staff.

8. *Powers and Duties of the Director General*

1) The Director General shall be the chief executive officer of the Center and shall, subject to the general directives of the Minister, direct and administer the activities of the Center.

፪· ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /፩/ የተጠቀሰው ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋናው ዳሬክተር፣
ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ የተመለከቱትን የማዕከሉን ሥልጣንና ተግባሮች ሥራ ላይ ያውላል፣
ለ) የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ መንግሥት በሚያጸድቀው መመሪያ መሠረት የማዕከሉን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፣
ሐ) የማዕከሉን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣
መ) የማዕከሉን የሥራ ክንውንና የሂሣብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚኒስትሩ ያቀርባል፣
ሠ) ተጠሪነታቸው ለዋናው ዳሬክተር የሆኑትን የማዕከሉ ኃላፊዎች በመምረጥ ለሚኒስትሩ አቅርቦ ያሾማል፣
ረ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ማዕከሉን ይወክላል፣

፫· ዋናው ዳሬክተር ለማዕከሉ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለማዕከሉ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

፱· የበጀት ምንጭ

የማዕከሉ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የሚገኝ ይሆናል፣
፩· በመንግሥት ከሚመደብለት ዓመታዊ በጀት፣
፪· ማዕከሉ ከሚያስከፍለው የአገልግሎት ዋጋና ሌሎች ክፍያዎች፣
፫· ከሌሎች ምንጮች ከሚገኝ ገንዘብ።

፲· የሂሣብ መዛግብት

፩· ማዕከሉ የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።
፪· የማዕከሉ የሂሣብ መዛግብት እና ሌሎች ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም በዋናው ኦዲተር በሚሰየም ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

፲፩· ደንብ ስለማውጣት

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለአዋጁ አፈጻጸም የሚረዳ ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

፲፪· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከጥር ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ·ም· ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ·ም·

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2) Without limiting the generality provided in Sub Article (1) herein above, the Director General shall
(a) exercise the powers and duties of the Cente specified under Article 6 of this Proclamation;
(b) employ, administer and dismiss personnel in accordance with directives approved by the Government in compliance with the basic principles of the federal civil services laws;
(c) prepare the work program and budget of the Center and implement same upon approval;
(d) prepare and submit to the Minister operational and financial report on the activities of the Center;
(e) select officials of the Center who are accountable to him and recommend them to the Minister for appointment;
(f) represent the Center in all its relations with third parties.

3) The Director General may delegate part of his powers and duties to other officials and employees of the Center to the extent necessary for the effective management of the Center.

*9. Source of Budget*

The budget of the Center shall be drawn from the following sources:
1) an annual budget allocated by the Government;
2) service charges and other fees to be collected by the Center;
3) money obtained from other sources.

*10. Books of Accounts*

1) The Center shall keep complete and accurate books of accounts.
2) The books of accounts and other financial documents of the Center shall be audited annually by the Auditor General or by an auditor designated by him.

*11. Power to Issue Regulations*

The Council of Ministers may issue Regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

*12. Effective Date*

*This Proclamation shall come into force as of the 31st day of January, 2002.*

*Done Addis Ababa, this 31st day of January, 2002.*

*GIRMA WOLDE GIORGIS*

*PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE